# አውደ ኢትዮጵያ

25 2008 | የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት አለው! | እትም 11

## የኢትዮጽያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች የፓርቲ አባል ባለመሆናችን የመሥራት ነፃነታችን ተገደበ፤ እድገትና ስልጠና እንዳናገኝ ተደረግን ሲሉ አማራሩ

በኢትዮጽያ ሬዲዮ የሚሰሩ ያነጋገርናቸው ጋዜጠኞች እንደገለፁልን በልማታዊ ጋዜጠኝነት ስም እና የብጥብጥ ዜና ለህዝብችን አይጠቅምም በሚል ሰበብ በአፍሪካ ምርጫዎች፤ በ ኢራንና በቻይና እንዲሁም በተለያዩ አለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ እንዳንሰራ ተከልክለናል ብለዋል። ሪፖርተሮች፤ የዜና አዘጋጆች እና የፕሮግራም አዘጋጆችን አነጋግረን እንደገለፁልን በድርጅቱ ዉስጥ መስራት የማነችልበት ደረጃ እየደረስን ነዉ ብለዋል።

ኢህአድግ እራሱ የሚያሰለጥናቸዉን ሰዎች እያመጣ አለቃ ያደርግብናል በሚሉት በነዚህ ጋዜጠኞች፤ ለ አባልንት ተጠይቀን እምቢ በማለታችን የተለያዩ ጫናዎች እየተደረጉብን ነዉ ይላሉ። በድርጅቱ ዉስጥ ደካማ የሆኑትን እያመረጡ አባል ያደርጋሉ፤ በድርጅቱ ዉስጥ ፋክክርና ፈጠራ እንዲጠፋ እያደረጉ ነዉ የሚሉት እነዚህ ጋዜጠኞች በቅርቡ በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ሰልጥነዉ የሚወጡ 160 በሬዲዮና በቴሌቪዥን የተለያዩ ክፍሎች ሊመደቡ እንደሆነ ይገልፃሉ። እንደምነጨቻችን ከሆነ በስራ ልምድ የሚገኝ እድገት ከቆመ አራት አመት አልፎታል።

ስሙ እንዳይገለፅ የጠየቀ የዜና አዘገጅ ባልደረባ እንደተናገረዉ ኤንባሲዎችና የዉጭ ሚዲያዎች ዜናዎችን ሞኒተር ስለሚያደርጉ ወዳጅነታችንን እንዳታበላሹብን፤ እኛ የመንግስት ቃል አቀባይ ስለሆንን የወዳጅ ሀገሮችን ክፉ ዜና አንሰራም፤ ሞያችሁን ማሳየት ከፈለጋችሁ ወደ ክልል እየወጣችሁ በልማት ስራ ላይ ስሩ እየተባልን ነዉ በለዋል። እንደምንጩቻችን ገለፃ የዜና ኤዲተር የተደረገዉ ያለምንም እረከንና ደሞዝ ጭማሪ ሲሆን ከሱ በኃላ ተቀጥረዉ በገዠዉ ፓርቲ አባልነት የተመዘገቡት በደሞዝና በእድገት እንዲበልጡት ተደርጓል።

ሌላዉ የፕሮግራም አዘጋጅ በበኩሉ እንኳን በፖሎቲካ ጉዳይ ላይ ይቀርና በመሃበራዊ ጉዳይ ላይ ለመሥራት እየተሸማቀቅን ነዉ ሲል ያማርራል። “ለምሳሌ ማህበራዊ ቀወስ ያስከትላል ብንል ስለጫት አሉታዊ ፕሮግራም ብንሰራ እጣችን እስከመባረር ይደርሳል። የአበባ ልማት በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለዉ ተፅእኖና ሊደረግ ስለሚገባዉ ጥንቃቄ በብዙ ልፋት የሰራሁት ፕሮግራም እንዳይተላላፍ ተደርጓል” የሚለዉ ይህ ጋዜጠኛ ባለን ችሎታና ፈጠራ መስራት አልቻልንም በአባልነት ጥያቄ እንድንማረር እየተደርግን ነዉ ብሏል። የኢህአእግ ነዉ የሚባለዉ እንኳን ሬዲዮ ፋና እንኳን ጋዜጠኞቹ በመህበራዊ ጉዳይ ላይ የፈለጉትን የመስራት ነፃነት አላቸዉ፤ እኛ ግን እጃችን ተይዟል ሲል አማሯል። በሪፖረተርነት መስራት ላይ ያለና ስሙ ለስራ ዋስትናዉ ሲል እንዳይገለፅ የጠየቀ የድርጅቱ ባልደራብ በበኩሉ “አንድ ስህተት (በለሱ መለኪያ) በቀጥታና በተዘዋዋሪ ያጠቁሃል፤ እንደፓርቲ አባል አስቀምጠዉ በሰራነዉ ስራ ሊያንጓጥጡን ይሞክራሉ፤ ለሪፖርቲንግ የሚልኩት ሰዉ አንድይነት ነዉ ይላል። እንደምንጫችን ገለፃ አባል ያልሆኑ ጋዜጠኞች ለሪፖርቲንግ ስራ የሚላኩት በራሳቸዉ ሰዎች ብቃት እስካላመኑ ድረስ ብቻ ነዉ።



ሌላዉ ያናገርነዉ ጋዜጠኛ በበኩሉ ዜና ለመስራት የሀላፊዉን ፈቃድ እንደሚጠይቅ ይናገራል። ምክንያቱም የሚመጣዉን ጫና በመፍራነትና ሥራዉን ላለማጣት ሲል የሚያደርገዉ ነዉ። እንደምንጫችን እምነት ይሄንን የሚያደርገዉ መንግስት ሳይሆን የተወሰኑ ሰዎች ፍላጎትም ጭምርም መሆኑን ነዉ። የቢሔራዊ ራዲዮ ተጠባባቂ ሀላፊዉ (አቶ ሰይድ ሙሄ) የፈለገዉን ዜና ማሳለፍ ያልፈለገዉን መጣል ሀላፊነት ቢኖረዉም ሥራ አስኪያጁን እየደወለ እያስፈቀደ ነዉ የሚሰራዉ። ይህም ቁጥጥሩ ምን ያህል እየጠነከረ እደመጣ ነዉ ያሳየዉ ባይ ናቸዉ።

በቅርቡ በሶማሌ ክልል የተነሳዉ የአንበጣ መንጋ ለመዘገብ የተነሳዉን ክርክር በማስታወስ የሚናገረዉ የዜና አዘጋጁ፤ አቶ ሰይድ እንዳይዘገብ እንደከለከለና የአንበጣዉ መንጋ ወደ ኦሮሚያ ሲጠጋ ቅድም ማስጠንቀቂያ መስጠት ነበረባቹ ተብለዉ እንደተገመገሙ ይገልፃል። ይህም በአለቆቹ መሀል እንኳን መግባባት እንደሌለ ያሳያል።

በኤፍ.ኤም አዲስ የሚሰሩ ጋዜጠኞች የአባልነትን ጥያቄ ባለመቀበላቸዉ የደሞዘም ሆነ የደረጃ እድገት እንደተከለከሉ ይገልፃሉ። ከአማራ ክልል ዜና አንባቢነት ተነስታ በኤፍ.ኤም 97 አስተባባሪ የሆነችዉ ወ/ሮ ፀሐይ ጫኔ በሞያዉ ብዙ እዉቀት የሌላትና ለፓረቲዉ ታማኝ በመሆኗ ቦታዉ እንደተሰጣት የሚገልፁት የድርጅቱ ባልደረቦች በቅርቡ የሚቀጠሩትም በየትኛዉ መስፈራት እንደሚቀጠሩ መቼ እንደተፈተኑ ሳይታወቅ ጣቢያዉን እየሞሉት ነዉ ይላሉ።

ያነጋገርናቸዉ ጋዜጠኞች እነደሚሉት ከ 90 በመቶ የሚሆኑት ሰራተኞች ሥራ በማፈላለግ ለይ ናቸዉ። ነገር ግን በግል የተከፈቱ ጣቢያዎች ዉስጥ መቀጠር አነችልም ምክንያቱም ባልተፃፈ ህግ ጣቢያዎቹ ከመንግስት ጣቢያዎች ጋዜጠኛ እንዳይወስዱ፤ የለቀቁንም ጋዜጠኞች እንዳይቀጥሩ አስማምተዋቸዋል።
በዚህ የተነሳ የተሻለ ደሞዝ የተሻለ የስራ ነፃነት ለማግኘት እንዳይችሉ በህገመንግስቱ የተሰጣቸዉ በነፃነት እየተዘዋወሩ የመስራት መብት እየተገደበ እደሆነ በማማረር ገልፀዉልናል።

በአሁኑ ሰዓት የመንግስት ጋዜጠኛ መሆን አስቸጋሪና የማይመረጥ ሥራ ነዉ የሚሉት ምንጩቻችን ባለፉት ሁለት አመታት ብቻ ከቲቪና ከሬዲዮ ብዙ ልምድ ያላቸዉ ጋዜጠኞች ለቀዉ እንደወጡና እነሱን የሚተካ ባለሙያ መጥፋቱን ገልፀዋል።

# የሰላማዊ ትግል ከአማራጭም በላይ ነዉ

## ርዕሰ አንቀጽ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የሶስት ሺህ ዘመን የነፃነት ታሪክ ያላት ነች። ይህ ታሪኳ ዛሬ በዕድገት መጥቀው፤ የዴሞክራሲ ተምሳሌት ተብለው፤ ከራሳቸው አልፈው የዓለምን ፖለቲካ ለመዘወር የበቁት ሀገሮች፤ እንደ ሀገር ከመታወቃቸው በፊት፤ መንግሥት ኖሯት በሀገርነት ታውቃ የኖረች መሆኗን ያሳያል። ነገር ግን ይህ የሶስት ሺህ ዘመን የነፃነት ታሪክ በአብዛኛው በጦርነት፤ ያውም በእርስ በርስ ጦርነት፤ የተሞላ ስለነበር፤ ኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ታሪኳን እያወሳች ባለችበት ስትቆም፤ ሌሎች በኢኮኖሚውም በፖለቲካውም ጥለዋት በመንጎዳቸው፤ ዛሬ እስዋ ከመጨረሻዎቹ ሀገሮች ተርታ የምትጠራ ሆናለች። በታሪክ የቀደመች፤ በስልጣኔ ኋላ የቀረች ሀገር፤ እንደ ዜጋ የሚያሳፍር ነው።

በየዘመናቱ በለስ ቀንቷቸው አልያም ጡንቻቸው ፈርጥሞ ለስልጣን የበቁትም ሆኑ 'በደምጥራት' እኔም ስልጣን ይገባኛል ብለው የሚነሱት አብዛኛዎቹ ወገኖች የቅድሚያ ትኩረታቸውና አላማቸው ስልጣን በመሆኑ፤ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ያልጎበኛት የረዥም ዘመን የነፃነት ባለቤት የጀግኖች ሀገር፤ ስልጣኔ የራቃትና ድህነት ስር የሰደደባት፤ ለሥልጣን ጦርነት የሚገጥሙ ቡድኖች የበዙባት ሀገር ለመሆን በቃች።

በጦርነት ወቅት ትኩረት የሚሰጠው ስለሚገኘው ድል እንጂ ስለሚጠፋው የሰው ህይወትም ሆነ ስለሚወድመው የሀገር ንብረት አይደለም። እንደውም ተቋማትን ማውደም፤ ድልድይና መንገድ ማፍረስና የሀገሪቷን ኢኮኖሚያዊ ሂደት ማዛባት፤ መንግስትን ማዳከምያ የትግል አንድ አካል ተደርጎ ነው የሚወሰደው።

በሥልጣን ላይ ያለው ሀይል ደግሞ፤ መጀመርያ ወደሥልጣን የመጣበትን መንገድ ስለሚያውቀው ኋላም እሱ በመጣበት መንገድ ሥልጣኑን የሚቀናቀኑ ብቅ ሲሉ ጭንቀቱን ስለሚጨምረው፤ ሙሉ ትኩረቱና ቅድሚያ ተግባሩ ሁሉ ሥልጣኑን ማስጠበቅ ይሆናል። ለዚሁ ተግባሩ በግልጽ የሚመድበው በጀት ይጨምራል። በይፋ በማይታወቅ ሁኔታ የሚወጣው ወጪ ይንራል። ልማትም ከአጀንዳ ውጭ ይሆናል።

ይህ ዓይነት መንግሥት ህዝብን አምኖና በህዝብም ታምኖ ለመኖር የሚያስችል መሰረት ስለሌለው፤ መንግስትና ህዝብ ሆድና ጀርባ ናቸው። ስለዚህም፤ ህዝቡ በሀገሪቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ፤ በሙሉና በነፃነት እይሳተፍም። ያለ ህዝብ ተሳትፎ ደግሞ ፖለቲካዊ መረጋጋትም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አይገኝም። ሥልጣን ላይ ያለው አካላም፤ ወንበሩ ላይ ለመቆየት ብቸኛ አማራጭ የሚያደርገው ጥበቃን ማጠናከር፤ የደህንነቱን ቁጥር መጨመርና፤ በህዝቡ ውስጥ ስጋትን መፍጠር ይሆናል። ይህ ደግሞ በራሱ፤ በህዝብና በመንግስት መካከል ያለውን ክፍተት በይበልጥ ያሰፋዋል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሀገር ወደ ዕድገት ልታመራ ስለማትችል ነው፤ ኢትዮጵያችን የሶስት ሺህ ዘመን የነፃነት ታሪክ እያወሳች የሀገሮች ሁሉ መጨረሻ ለመሆን የበቃችው። ስለሆነም ይህ ሂደት አንድ ቦታ ላይ ሊገታ ይገባዋል። ለሥልጣን ሲባል ወንድም ወንድሙን ገድሎ የሚፎክርበትና ሀውልት የሚያቆምበት፤ ልጅ በአባትና በእናቱ ላይ የሚተኩስበት ለሗላ ቀርነታችን አንዱ ምክንያት ሆኖ የኖረው ተግባር ዛሬ ማብቃት አለበት።

ለሥልጣን ሲባል፤ የተገነባው እየፈረሰ፤ ሀገራዊ መሰረቶች እየተናዱና በለስ ቀንቶት ለሥልጣን የሚበቃው ሁሉ ከዜሮ የሚጀምርበትና በራሱ የዕይታ መጠን ሀገሪቱን የሚቃኝበት ሁኔታ አብቅቶ ትውልድ ተሻጋሪ የሆነ ሀገራዊ አስተሳሰብ የሚፈጠርበት፤ በሄደ በመጣው የማይናወጥ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት የሚገነቡበት ሂደት ዛሬ መሰረቱ መጣል አለበት። ይህን ማድረግ ካልቻልን ነገም እንደዛሬው የሶስት ሺህ ዘመን ባለታሪክ፤ ግን ከሥልጣኔ የራቅንና ድህነት ቤቱን የሰራብን እንደሆንን እንኖራለን።

እንደ ረዥም ዘመን ባለታሪክነታችን፤ በልማት አለማደጋችንና ዲሞክራሲን እንደናፈቅን መኖራችን ከምር የሚያስቆጨን ከሆነ ለዚህ ምክንያት ከሆነው የመገዳደል አባዜ መላቀቅ አለብን። ትግሉም ለሥልጣን ሳይሆን መሰረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ ሰላማዊ ትግል መሆን አለበት። ለዚህም ነው ሰላማዊ ትግል ከአማራጭም በላይ ነው የሚባለው።

በሰላማዊ ትግል ሂደት መገደል ይኖራል። መገዳደል ግን አይኖርም። ሰላማዊ ትግል ልዩነትን ለማስፋት ሳይሆን፤ ለመቻቻል በር የሚከፍት ነው። ሰላማዊ ትግል ለአሸናፊነት ሲበቃ በቀል አያስተናግድም። ለጥላቻም ቦታ አይኖረውም። በመሆኑም የተበላሸውን አስተካክሎ፤ የጎበጠውን አቅንቶ፤ በነበረው ይቀጥላል እንጂ ሁሉንም አጥፍቶ ከዜሮ ልጀምር አይልም። ሰላማዊ ትግል ለአጭር ጊዜ ለሚገኝ ለሥልጣን የሚያበቃ ድል ሳይሆን ትውልድ እየገነባው የሚሄድ መሰረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ነው የሚታገለው። ይህም በመሆኑ ዕይታው አጭር አይደለም። በጠባቡ አያስብም። በቶሎ ተስፋ አይቆርጥም።

በዚህ ትግል ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች፤ ይልቁንም ይህን ትግል የሚመሩ ግለሰቦችና ስብስቦች በቅድሚያ ሰላማዊውን ትግል ምርጫቸው ብቻ ሳይሆን፤ በምንም አይነት ሁኔታ የማይመቻመች መርሀቸው ሊያደርጉት ይገባል። እምነት በፅናት የሚያቆራኙት ሲሆን፤ ምርጫ ግን ባልመሰለ ጊዜ የሚተውት ነውና።

የሦስት ሺህ ዘመን የነጻነት ታሪክ እያወሳን፤ ድህነትን እንደፈጣሪ ስጦታ ተቀብለን መኖር የሉብንም ካልን ከሰለማዊ ትግል ውጭ ምርጫ የለንም።

ለህዝባዊ ስልጣን ለድል የሚያበቃው የዕምንት ቃል ኪዳን የሰላም ትግል ነው፤ ትግሉ ቢጠነክር ቢከብድ መስዋዕቱ የማይናወጥ ነው የታጋይ ጽናቱ።

# "ፓርላማ ያለመግባት ውሳኔ የብዙዎች ውሳኔ ነበር ማለት አይቻልም»

አቶ ተመስገን ዘውዴ በጎፋ ክፍለ ሀገር ሳዎላና ቡልቂ አካባቢ ተወልደው አድገዋል። እዛው በተወለዱበት አካባቢ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።በአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በቢሮ አስተዳደር ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን በት/ቤቱ ባስመዘገቡት ውጤት እዛው በአስተማሪነት ተቀጥርው ለአራት አመታት አገልግለዋል። አሜሪካን አገር በመሄድ በቴክሳስ ግዛት በግል ኮሌጅ ውስጥ በንግድ ሥራ አስተዳደር የመጀመሪያ ድግሪያቸውን ያገኙት አቶ ተመስገን እዛው በተማሩበት አሜሪካ ቴክሳስ በሚገኝ የነዳጅ አውጭ ድርጅት ተቀጥረው እስከ 1995 እ.ኤ.አ ሰርተዋል።በዛው አመት ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በአድማስ ዩኒቨርሲቲ ክኮሌጅ በዲንነት በሌክቸረርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።



አቶ ተመስገን ዘውዴ

በ 2005 እ.ኤ.አ በተደረገው ሀገራዊ ምርጫ ቅንጅትን ወክለው ተወዳድረው በፓርላማ አባልነት የተመረጡት አቶ ተመስገን በፓርላማ የቀድሞ ቅንጅት ተጠሪ በመሆን እየሰሩ ነው።ቅንጅት ፓርላማ ላለመግባት ወስኖ እያለ እርሳቸው የሚሚመሩት ቡድን ለምን ፓርላማውን ተቀላቀለ? ፓርላማ በመግባትስ ያስገኙት ለውጥ ይኖር ይሆን?ስንል አነጋገርናቸዋል።

ጥያቄ፡ አቶ ተመስገን ፖለቲካን የት ጀመሩ? ለምን?

መልስ፡ ከፖለቲካ ቤተሰብ ነው የተገኘሁት።አያቴ በአጼ ኀ/ሥላሴ ዘመን ከሃመር ባኮ አካባቢ ተመርጠው ለሁለት ተርም የፓርላማ አባል በመሆን ሰርተዋል። አባቴም እንዲሁ የህዝብ አገልጋይ ስለነበሩ የነሱን ፈልግ በመከተል የፓርላማ አባልና ፖለቲከኛ የመሆን ፍላጎት ነበረኝ።ብዛውም ላይ የሀገራችን ሁኔታ የብዙዎቻችንን ተሳትፎ የሚጠይቅ ሆኖ ስላገኘሁት ፖለቲካ ወስጥ ልገባ ችያለሁ።የመጀመሪያ እድልም በ2005 ምርጫ ለመጠቀም በማሰብ በግሌ ለመወዳደር የሚጠይቀውን ፎርማሊቲ ካሟላሁ በኋላ አቶ ልደቱ ቢሮዬ ድረስ በመምጣት የኢደፓን መተዳደሪያ ደንብና የፖለቲካ ፕሮግራም አንብቤ ከተስማማኝ ከእነሱ ጋር እንድወዳደር ጠየቀኝ በዚሁ መሰረት የሊበራር ዴሞክራሲን መርህን የሚከተሉ መሆኑን ከተረዳሁ በኋላ አባል ሆኜ ለተወሰኑ ወራቶች ቆይቻለሁ። ፓርቲው ቅንጅትን ሲቀላቀልም በመሀል መርካቶ እንድወዳደር ተመድቤ ከፍተኛ ድምጽ በማግኘት አሸንፌ ፓርላማ ገብቻለሁ።

ጥያቄ፡ ኢደፓ እናት ፓርቲዎ ከሆነ ታዲያ ለምን በዛው አልቀጠሉም?

መልስ መስከረም 14 በተደረገው ውህደትና የእናት ፓርቲዎች መክሰም ምክናይት ከዛግዜ ጀምሮ የቅንጅት አባል መሆናችንን በመቀበል ህዝቡም የሚያውቀን የተወዳደርነውና ያሸነፍነው ምርጫ ቦርድም የሰጠን መታወቂያ ቅንጅት የሚል በመሆኑ፤እኛም ራሳችንን የምንቆጥረው በቅንጅት ስም በመሆኑ በዛው ፅንተን እየታገልን ነው።

ምርጫ ምልክታችን ለሌላ ፓርቲ፤ ስማችን ለተወሰኑ ግለሰቦች እስኪሰጥ ድረስ በዚሁ ፅንተን ቆይተናል።በአሁኑ ሰዓት በፓርላማ ያለን 42 የምንሆን የቀደሞ ቅንጅት አባላት ምልክታችንና ስማችን ለሌላ ቢሰጥብንም ከእስር ከተፈቱት አመራሮቻችን ጋር በመሆን አንድነት ለዲሞክርሲና ለፍትህን አቋቁመን ሰላማዊ ህዝባዊ ትግሉ እንዲቀጥል የራሳችንን አስትዋጽኦ በማድረግ ላይ እንገኛለን።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ፓርላማ ያለመግባት...

ከገጽ 2 ያዞረ

ጥያቄ: የቀድሞ ቅንጅት እንዲህ ለምን ለመበታተን አበቃው?

መልስ: ትልቁ ምክናይት የገዢው ፓርቲ ስጋት ነው። ቅንጅት በአጭር ግዜ ውስጥ ለህዝብ ስሜት መነሳሳት ምክንያት በምሆኑ በአጭር መቀጨት አለበት ብሎ ስለተነሳ ነው። ቅንጅት በስምንት ወራት ዕድሜው ሌሎች ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ፓርቲዎች ያልሰሩትን በመስራቱ፤የፖለቲካ የማህበራዊና ኢኮኖማዊያዊ ፕሮግራም ይዞ በመቅረብ በህዝብ ተቀባይነት በማግኘቱ ገዢው ፓርቲ ቅንጅት እንዲፈርስ አባላቶቹ እንዲበታተኑ፤ ደጋፊዎቹ ስጋት ውስጥ እንዲገቡ በማደርጉ ነው።ቅንጅትን በመከተል በመደገፍ ሊመጡ የሚችሉ ጫናዎችን በመፍጠሩ፤ የድርጅቱ መሪዎች አባላቱና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎች ለመታሰራቸው ለመበተናቸው ለመሰደዳቸው ቀጥይ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎች ይህንን ተፅኖ መቋቋም እንዳይቻል ገዢው ፓርቲ ያደረሰው ተፅኖ ከባድ ነበር።

ሌላው ቅንጅት እንደፓርቲ ይህንን ተፀኖ ለመቋቋም የሚያስችል ድርጅታዊና ፖለቲካዊ ህይወቱ በአጭር ግዜ የመጣ እንደመሆኑ፤ ያለፈ ልምዶችን ምርኩዝ ማድረግ አለመቻሉ፤ በደረሰበት ጥቃት በቶሎ መፍረስ ችሏል።

ጥያቄ: የቀድሞ ቅንጅት ህዝብን አወያይቶ ፓርላማ ላለመግባት ወስኖ እያለ እናንተ ገብታችኋል በውሳኔው አልተስማማችሁም ነበር ማለት ነው?

መልስ: ውሳኔው የተበታተነ ውሳኔ ነበር። ቅድም እንዳአልኩህ ድርጅትዊ መሰረት ባለመኖሩ ከገዢው ፓርቲ የሚመጡ ተፅኖችን መቋቋም አልተቻለም የቅንጅት አመራሮች እስር ቤት ሲገቡ ቀጣይ አመራሮች ይኖራሉ የሚል ግምት ነበር። እነዚህ አመራሮች ግን አልታዩም የነበሩትም ሳምንት ባልሞላ ግዜ ውስጥ ካንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ሲደበቅ የተያዘ አመራር ነው። ለፓርላማ ተመራጮች አመራር ሊሰጥ የሚችል አካል አልነበረም።

ፓርላማ እንግባ አንግባ የሚለውን ውስኔ በአንድነት ተሰብስበን ሳይሆን በግል ነው የወሰነው አንዳንዱ በግል ህይወቱ ምክንያት አንዳንዱ በገዢው ተፅኖ ሌላው ደግሞ ህጋዊና ሰላማዊ ትግሉ መቀጠል አለበት ብሎ በመወሰኑ ነው ፓርላማ የገባነው። ጥቂት አመራሮች በመታሰራቸው ትግሎ መቆም የለበትም ፤ ትግሉ የሰዎች ሳይሆን የህገር ነው። በሚል ስሜት ነው ፓርላማ የገባነው።ትግሉ ታጋዮች ገነው የውጡበት በመሆኑ እንጂ የግለሰብ አይደለም።የዚህ አይነት አመለካከት ያላቸው ጥቂት ናቸው። አብዛኛው ህዝብ ትግሉ እንዲቀጥልለትና አማራጭ እንዲኖረው ነው የፈለገው።

ጥቂት የህገር ሽማግሌዎች፤ጥቂት ታዋቂ ግለሰቦችን፤ ጥቂት ጋዜጠኞችና አነጋግሮ ፓርላማ አትግቡ ማለት አይቻልም። የኢትዮጵያ ህዝብ 80 ሚሊዮን ነው። የእነዚህን ህዝቦች ፍልጎት የሚያንፀባርቅ ሂደትን ጥቂት ሰዎችን በማማከር የሚወሰን አይደለም። ጉዳዩም እስር ቤት የገቡት ግለሰቦች ሳይሆን የትግል ጉዳይ ነው። በዚህ አምነን ነው ፓርላማ የገባነው።ወደፊትም ታጋዮች ሳይሆኑ ትግሉ ለህዝብ የሚሰጠው ጥቅም ገኖ እንዲወጣ ነው የምንሰራው።በዚህ መስፈርት ለኢትዮጵያ ህዝብ ይጠቅማል ያልነውን ትግል በፓርላማ ውስጥ ለሠላም ለዲሞክራሲ ለልማት ጥቅም ይኖረዋል ያልናቸውን ህጎች በማሳለፍ አይጠቅምም ያልነውን በመቃወም ሦስት ዓምት አሳልፈናል።

ጥያቄ: ስለዚህ ውሳኔው ትክክል አይደለም ብላችሁ ታምናላች

መልስ: የዲሞክራሲ ሂደቱ የሚጠይቀው ይህንኑ ነው የተወሰኑ ሰዎችን በማምለክ የሚወሰን ውሳኔ መከተል ሳይሆን የሊብራል ድምክራሲን በምንከተል ሰዎች የምናምንበትን እንድንፈፅም ይፈቅዳል። በርግጥ ይህ የፓርቲ ዲሲፕሊን ጉድለት ሊኖርበት ይችላል ሆኖም ግለሰቦቹ ፓርላማ መግባታችን ትክክል ነው ብለውና በምክንያታቸው አምነው ገብትዋል።

ጥያቄ: እንደግለሱብ ይለያያል ሲሉ ተሰብስባችሁ አልተነጋገራችሁም? ህዝቡንስ አላማከራችሁም?

መልስ: ህዝቡን ያነጋገሩት ጥቂት የፓርላማ ተመራጮች ናቸው።ህዝብ የሚባሉትም በተጠራው ስብሰባ ላይ የተገኙ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ናቸው።

ጥያቄ: ፓርቲው በራሱ ድምፅ ሰጥቶበት ፓርላማ ላለመግባት ወስኖ አልነበረም ወይ?

መልስ: ይሄ ውሳኔም ቢሆን የፓርላማ ተመራጮች የተሳተፉበት አልነበረም።ቁም ነገሩ የፓርቲ ዲሲፕሊን ተጥሷል አልተጣሰም የሚለው እንዳለ ሆኖ ግለሰቦች አምነውበታል። ውሳኔውም ያሳለፉበት የየራሳቸው ምክንያት አላቸው። ምናልባት ይሄ ውሳኔ ትክክል ነው አይደለም የሚለውን በፓርቲ ዲሲፕሊን የምናየው ይሆናል።

ጥያቄ: ፓርላማ የገቡ ተቃዋሚዎች የኢአሃድግ የይስሙላ መድብለ ፓርቲ እያስፈፀሙ ነው ቢሎት መልሶ ምን ይሆናል?

መልስ: ይህን ራሱ ማወቅ የሚቻለው ፓርላማ በመግባት ነው። የኢህድግ ሥርአት አፋኝ መሆኑን በፓርላማ የዲሞክራሲ ስርአት እንደሌለ በአብላጫ ስም ድምፅ ስም አባገነን እንደሆነ ማወቅ የሚቻለው እዛው ገብተው ሲያዩ ነው። አንተ አሁን ይህንን የምትጠይቀው እኛ ፓርላማ ውስጥ በመሆናችን ነው። እኛ እዛ ባንገባ በተጨባጭ ማስረጃ ሳይሆን በአሉባልታ ነበር የምታውቀው።እኛ ገብተን አይተን ህዝቡ እንዲያውቀው እያደረግን ነው። ፓርላማ የመግባት ትልቁ ጥቅምም ይኸው ነው።

ኢህአድግ ለመድብለ ፓርቲ ሥርአት መስፋፋት ፍላጎት እንደሌለው መድረኩ ይህን አጋልጠ እንዲያሳይ አድርገናል። መግባታችን ኢፍትህዊነቱን፤የፖለቲካ ሜዳውን እያጠበበ መምጣቱን ለማወቅ አስችለናል።

ጥያቄ የሚያወጣቸውም ህጎችም እኮ ይህንን ያረጋግጣሉ። ፓርላማ አንገባም የተባለውም ለመድብለ ፓርቲ የሚመች ሜዳ ይመቻች፤በዚ ሁኔታ ብንገባም መሰራት አንችልም ብለው ነው ?ምናልባት የድምፅ መዘረፍ እንዳለ ሆኖ ተጠይቆ የነበረው ቅድመ ሁኔታ ቢሟላ ኖሮ ሁሉም ፓርላማ ይገባ ነበር።መንግስት ጥያቄውን አለመቀበሉና ተጨማሪ ህጎችን ማውጣቱ ለኢፍታዊነቱ ማሳያ በቂ አይሆንም?

መልስ: ፓርላማ ከመግባታችን በፊት ከተነሱ ነጥቦች አንዱ የፓርላማ አሰራርና ሥነ-ምግባር ደንብ እንዲሻሻልና የሌሎች ሀገሮች ልምድ እንዲካተት የሚል ነበር።እኛም ይሄ በከፊል እንዲሻሻል አድርገናል።ፓርላማ ከመግባታችን በፊት የነበረው ቋሚ ኮሚቴና በኮሚቴው ውስጥ ያሉ አባላት ቁጥር እንዲጨምር አድርገናል።ከ 13 ቋሚ ኮሚቴዎች ውስተ አንዱ (በመንግስት ወጪ ተቆጣጣሪ ቋሚ ኮሚቴ) በተቋሚዎች እንዲያዝ አድርገናል።

ጥያቄ ባለፉት ሦስት አመታት በፓርላማ ቆይታችን አምጣነው ፤አስገኘነው የምትሉት ለውጥ አለ?

መልስ: አንዱና ዋነኛው የመቻቻል ፖለቲካ እንዲኖርና፤ሰላማዊና ህጋዊ ትግሉ እንዲቀጥል፤የመቻቻል ፖለቲካ እንዲኖር አስተዋፆ ይኖረዋል ብለን እናምናለን። ሆኖም እኛ እዛ በመግባታችን በኛ ሀሳብ ተሻሽሎ ወቷል የምንለው አንድም አዋጅ የለም። ምክንያቱም ነገሮች የሚወሰኑት በአብላጫ ድምፅ ስለሆነ ኢህአድግ ደግሞ ያን ድምፅ ስለወሰደ፤አባላቶቹ የፈልገው ክርክር ቢኖር እንደ አንድ ሰው ስለሚመረጡ፤ባለፉት ሦስት አመታት የወጡት ህጎች የኢህአድግን ፍልጎት የሚያንፀባርቁ ናቸው።የኛ ፍላጎትና ሀሳብ ተካቶ የወጣ አንድም አዋጅ የለም።

ጥያቄ: ፓርላማው ገዢው ፓርቲ የሚፈልገውን ህግ የሚያፀድቅበት፤የህገርና የህዝብን ሰበአዊ ፤ ዲሞክራሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን የሚያረጋግጡ፤ የሚያደንቁፉ ህጎች ሲፀድቁ የሚታይበት የመረጣችሁን ህዝብ ውክልና ለማረጋገጥ የማይቻልበት ሸንጎ አብል በመሆኖ ምን ይሰማዎታል?

መልስ: በፓርላማ አብላጫ ድምፅ ወስዶ የምያወጣቸው ህጎች አብዮታዊ ዴሞክራሲን የተከተሉ፤ የነሱን ፍላጎት ብቻ የሚያንፀባርቁ መሆናቸው ቅሬታ ይሰማኛል። ሆኖም እኛ የምናነሳቸው ሀሰቦችና ክርክሮች ቀስበቀስ የህዝቡን ንቃተ ህሊና የሚያዳብሩ ነው እየሆኑ ያሉት። የዚህ ንቃተ ደግሞ በምርጫ ወቅት መገለፁ አይቀርም።

ኢህአድግ ባለፉት ስድስት ወራት የብሄራዊ ባንክ፤ የምርጫ ቦርድ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማቋቋሚያ፤የፕሬስ አዋጆችን አፅድቋል።እነዚህ ህጎች ኢህአድግ ራሱ ያፀደቀውን ህገ-መንግስት የሚጣረሱ የህዝብን መብት የሚገድቡ ናቸው። እኛም በተሰጠን አንድና ሁለት ደቂቃ እነዚ ህጎች የህዝብን ስሜት የማያንፀባርቁ የጨቋኝና አፋኝ ስርአት መገለጫ መሆናቸውን ህዝቡ እንዲያውቀው እንደርጋለን። ይህም በምርጫ ወቅት ትልቅ አስተዋፆ ይኖረዋል።ስለዚህ የኛ እዚያ መግባት የህዝብ ንቃት እንዲጨምር ምን እየተሰራ እንደሆነ እንዲያውቅ እያደረግን ነው።

ጥያቄ ከፓርላማ የአማካሪ አባልነትና ከቋሚ ክሚቴ አባልነት ተነስታችሁ ቦታው ለነ አቶ አየለ ጫሚሶ ትሰጥቷል።እናንተ 42 ሆናችሁ ቦታችሁ ለሦስት ሰው ሲሰጥ ህጉ ምን ይላል?እናንተስ ውሳኔውን ለመቀበልበስ ምን አደረጋችሁ?

መልስ: እንደሚታወቀው የዚህ መንግስት አካሄድ የጉልበት ሀይል ነው። እኛ ሚያዚያ 30 ቀን በአፈጉባኤ በኩል ያስገባነው የኢትዮጵያ መሬት በሱዳን ተይዟል፤ ዜጎች ተፈናቅለዋል የሚለውን ጥያቄ በግንቦት 13 ቀን ጠ/ ሚኒስትሩ በፓርላማ ቀርበው ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ በሰጡበት ወቅት ጥያቂያችንን ወስደው የርሳቸው አባል እንድያነበው አድርገዋል። እኔም ይሄ ጥያቄውን የራስችሁ አድርጋችሁ ማቅረብ አግባብ አይደለም ብዬ ተቃውሞዬን በማሰማቴ በፓርላማ የመንግስት ተወካይ ዝተውብኛል። ቢሮአቸው ጠርተው በዛቻ መልክ አርፈህ ልጆችህን አሳድግ ብለውኛል። ከዛን ቀን ወዲህም በምክር ቤቱ የነበረንን ቢሮ እንድንለቅ፣ ባሉት 13 ቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ የነበረንን ውክልና እድናጣ፤ እኔም ከፓርላማ ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ እንድለቅ ተወሰኖብኛል።(በፓርላማው የመንግስት ተወካይ አቶ ሽፈራው ጃርሶ ናቸው)

ውሳኔው ፍትሀዊ እንዳልሆነ በመግለፅ ገለልተኛ ይሆናሉ ብለን አፈጉባኤውን ብንጠይቅም ውሳኔውን ከመድገም ሊረዱን ፍቃደኛ አልሆኑም። በፓርላማ ያለን ቁጥር ብዙ ስለሆነ እስካሁን ለሁልም አልተነገራቸውም። እኔን ግን አሰወጥተውኛል። ውሳኔውን በደብዳቤ እንዲሰጡኝ ብጠይቃቸው አፈ-ጉባኤ ደብዳቤ አይፅፍም ብለው ንገሩን ለመዘጋት ሞክረዋል። አባላቶችህን ይዝህ ውጣ ብለው ነግርውኛል።

ጥያቄ: እስካሁን አልወጣችሁም ማለት ነው?

መልስ: እኔን አሰወጥተውኛል አባላቶቻችን ግን ምክር ቤቱ ለእረፍት እስኪበተን ድረስ የፅሁፍም ሆነ የደብዳቤ መልክት ስላልደረሳቸው ባሉበት እየሰሩ ነበር። ከዛን ቀን ጀምሮ የሚሰጠን ደቂቃ ተቀንሶ ሀሳባችንን ለመግለፅ አልቻልንም።

ጥያቄ: በፊት አራት ደቂቃ ነበር የሚሰጣችሁ ክሱ ላይ ነው የተቀነሰው?

መልስ: አዎ በፊት የሚሰጠን እንደ ፓርቲ በአባላቶቻችን ብዛት ትስቦ ነበር። አሁን ግን እንደአንድ ሰው ታስበን አንድ ደቂቃ ነው የሚሰጠን። በምክር ቤቱ 42 መቀመጫ በመያዙ ከተቀዋሚዎች ክፍተኛውን ቁጥር ብንይዝም ያሉብን ጫና እየበረታ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 31 የሚፈቀድልንን የመደራጀት መብት ተፍገን የምክር ቤት ሀላፊነታችንንና የህዝባችንን ውክልና ለማረጋገጥ አልደረስንም።

ጥያቄ: በእንዲህ አይነት ሁኔታ መስራት ምን ስሜት ይሰጣል?

መልስ: በጣም የሚያሳዝን ነው። ለራሴም ለምወክላቸው የፓርላማ አባላትም ሆነ ለህዝቡ በነጻነት የመናገር መብቱ ሲገፈፍ ማየት የምያሳዝን ንው። በህገመንግስቱ የተሰጠን

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ፓርላማ ያለመግባት...

ከገጽ 3 የዞረ

መብት እንዲከበር በምንታገልበት ሌሎች ሀሰባቸውን በነጻነት እንዲያጸባርቁ ለማገዝ ይቅርና በኛ ላይ አሉታዊ በሆነ መንገድ እየተተረጎመብን ህስባችንን በንጻነት መግለፅ እንዳንችል ተደርገናል።እኔ በፓርላማ ውስጥ በምናገረው ነገር እንድሸማቀቅ አፈ ጉባኤው ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠኝ እየተደረገ ነው።ከገዢው ፓርቲ አባላት ጭምር ዛቻ ማስፈራሪያ እየደረሱብኝ ነው ያለሁት።ሁላችንም በህገ-መንግስቱ የተሰጠንን መብት እየተገደበ ነው ያለው።ስለዚህ ፓርላማ መሄድ ያመኑበት ተነግሮ ሌሎችን አስምኖ ለሀገር የሚጠቅም ህግ ለማውጣት የማይቻልበትና ሁላችንንም የሚያሸማቅቅ ሆኖ ነው ያገኘሁት።

ጥያቄ: ገዢው ፓርቲ አብላጫውን ድምፅ በንጥቂያ ወስዷል፤ አባላቱም መረጠን ለሚሉት ህዝብና ልህሊናቸው ሳይሆን ለፓርቲያቸው ነው ታማኝነታቸው። እናንተ ደግሞ ለህዝብና ለህሊናችሁ ስትሉ ትከራከራላችሁ ሰሚ አታገኙም በዚህ ሁኔታ ፓርላማው የሞራል ተጠያቂ ነው ብዬ አስባለሁ እርሶስ ምን ይላሉ?

መልስ: ልክ ነው።ህገ-መንገስቱ በአንቀፅ 54 ን/አንቀፅ 4 አንድ የፓርላማ ተመራጭ ተጠያቂነቱ ለመረጠው ህዝብና ለህሊናው ነው ይላሉ።ህዝብና ለህሊናው ነው ይላሉ። ለፓርቲው ነው የሚል አንድም ቦታ የለም።ነገር ግን የኢህአድግ አባላት ከፓርቲያቸው ውጭ እንዲያስቡ ተፅኖ ይደረግላቸዋል።ይህንንም ባለፉት ሦስት አመታት አረጋግጠናል። የሚያንፀባርቁት አብዮታዊ ዲሞክራሲን እንጂ ለህገ-መንግስቱና ለመረጣቸው ህዝብ ወይም ለህሊናቸው ተገዢ ሆነው አይደለም።

እኛም በዚህ በኩል ተጠያቂ ነን። ምክንያቱም በሌሎች ሀገሮች በፓርላማ ክርክር አብላጫ ድምፅ ቢኖርህም ዝቅተኛ ድምፅ ያለው ፓርቲ ያመጣው ሀሳብ ከተስማማህ ድምፅህን ለዚህኛው ወገን መስጠት ትችላለህ። እዚህ ግን በማንኛውም የድምፅ አሰጣጥ ሂደት መንግስት ተወካዩ ሁሉም አባላቶቻቸው እጅ ማውጣታቸውን ያረጋግጣሉ።ሌላው በጣም የሚገርመው በኛ ፓርላማ በሚስጥር ድምፅ መስጠት አይፈቀድም።

ጥያቄ: ምክንያቱ ምንድን ነው

መልስ: ምክንያቱ የገዢው ፓርቲ ተወካይ አባላቶች እንደ አንድ ሰው መምረጣቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። በሚስጥር ቢመርጡ ከተቀዋሚ ጋር ያብራሉ ብለው ስለሚስጉ ነው።ስልዚህ እኛ የዚህና የአብላጫ ድምፅ ስም ተጠቂዎች ነን።

ጥያቄ: ብዙ ግዜ በኢኮኖሚ ጉዳይ ላይ ክርክር ያደርጋሉ ለምን ይሆን?

መልስ: ይህን የማደርገው እኮኖሚው ብሚይውቁ ሰዎች እየተመራ ባለመሆኑ ነው። የ 5 እና የ 6 ቢሊዮን ዶላር GDP በጣም ትንሽ ኢኮኖሚ ነው ብዙ እውቀት አይጠይቅም።ነገር ግን ሰዎች በግምት በይሆናል ነው የሚመሩት። በዚህ ሀላፊነት ላይ ይሉ ሰዎች ኢኮኖሚውን መምራት የሚያስችል ልምዱም እውቀቱም እንደሌላቸው ለመረዳት ይቻላል።ለምሳሌ በከተሞች አካባቢ የዋጋ ንረት ከሁለት አመት በፊት ምልክት ማሳየት መጀመሩን፤ ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን ስለሚችል የጠቅላላ አቅርቦቱንና ፍላጎቱን አስተካክሉ ስንላቸው አላወቁትም ነበር ። እንዲያውም በፌዝ መልክ ነበር ያዩት።አሁን ግን ትኩረት ሰጥተው አንዴ ነጋዴውን አንዴ ገበሬውን እያሰሩ ነው ።አሁንም ችግሩ የት እንዳለ አላወቁትም። ለነሱ ትልቅቁ ሳይንሳዊ ግኝት የህብረት ሱቅ መክፈት ነው።ይሄ ደግሞ ከደርግ ጊዜ ጀምሮ የነበረና የማያዋጣ መፍትሄ ነው።

ጥያቄ እንፍሌሽኑ እየተባባሰ በአንዳንድ ክልሎች 45 ፐርሰንት የደረሰበት አለ። መፍትሄው ምንድነው?

መልስ እንደኔ ሀሳብ አሁንም ኢኮኖሚውን ይመራሉ የተባሉ ሰዎች አሰናብቶ ሌሎች ክፍት የሆነ ጭንቅላት ያላቸውን፤ ልምድ ያካበቱ በራሳቸው ሀሳብ የማይደርቁ ሰዎችን መተካት ችግሩን ያቃልለዋል።

ጥያቄ: ኢህድግ የዶክተር መራራን ቃል ልወሳና አፍ እንጂ ጆሮ የለውም ስለዚህ ፓርላማ ከመግባት ቀድሞ ጆሮውን እንዲኮርኮር ማድረግ አይቀድምም?

መልስ በዚህ አጭር ጊዜ ልምዳችን ያየነው ገዢው ፓርቲ ስህተቱን የማመን፤ ምክር የመቀበል የመጠየቅ ልምድም ታሪክም የለውም። ስህተትን እንደሞት የሚያይ የአብሪት አመለካከት የተጠናወተው ፓርቲ ነው። ከስህተቱ ተምሮ በቅንነት አዋቂዎችን ማሳተፍ አይፈልግም።ሆኖም ፓርላማ መግባቱ የሰላማዊና የህጋዊ ትግሉ ዋነኛ አካል ነው። ዝቅተኛ ድምፅ ያለንን ሀሳብ ያለመቀበል፣ቢቀበልም እውቅና ያለመስጠት ችግር አለበት። እንዲያም ሆኖ ትልቁ ችግሩ አለማዳመጡ ነው።ቢያዳምጥ ትልቁ መድረክ ፓርላማ ነው።ሳይገቡ መከራከር ብች ሳይሆን ገብቶም ሀሳቦአቻችንን እንዲቀበል መታገል ያስፈልጋል።

ጥያቄ: በዚህ ሁኔታ ሦስት አመት ቆያችሁ አሁንም ህጋዊና ሰላማዊ ትግሉን እንቀጥላለን ትላላችሁ ኢህአድግ ባያያዙ ቢቀጥልና ለውጥ ማምጣት ባትችሉ ህዝቡ በናንተ ተስፋ አይቆርጥም?የተቃውሞ ፖለቲካውንስ አያዳክመውም?

መልስ: የህዝብ የዲሞክራሲ ፍላጎት በአጭር ጊዜ እንዳይዳከም ለማድረግ የእኛ ስራ መሆን አለበት።ይሄ ደግሞ በሂደት ነው የሚመጣው ቢያንስ በህገ-መንግስቱ የተሰጠንን መብት ማስከበር ብንችል መልካም ነበር።አህን ያለንበት ሁኔታ ግን ግዜ የሚፈጅ ትግል ሆኖል።ይህንን ትግል ማቀጣጠል ያለብን እኛ የተቃውሞ ፖለቲከኞች ነን።

የህዝብ መንፈስ እንዲበረታታ፣ ተስፋ እንዳይቆርጥ እዚህ ሂደት ውስጥ የገባነው ለአጭር ግዜ አለመሆኑን እንዲረዳ ማድረግ የኛ ሀላፊነት ነው። ኢትዮጵያ ከአለም ካሉ ሀገሮች ህዝቦቿከአለም ህዝቦች እኩል ሀሳባቸውን የሚገልፁበት፤የሚደራጁበት መረጃ ያለገደብ የሚለዋወጡበት ሀገር እንድትሆን ረጅም ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የማስተማር የሂደቱ አጋር እንዲሆን ማድረግ ሃላፊነትና ግዴታ አለብን።በዚህ ሂደት የራሳችንን ሚና በሚገባ ከትወጣን ውጤት ላይ የመድረስ ተስፋ አለን።

ጥያቄ: መንግስት አፋኝና ጨቋኝነቱን እያሰፋ፤የህዝብ ችግር እየተባባሰ የእናንተን ረጅም ትግል እንዴት ይታገሳል?

መልስ: አብዛኛው የአለም ሀገራት በዲሞክራሲያዊ ሂደት እየተመሩ መረጃን ኮምኒኬሽን የህዝብ ሀይል እየሆኑ፤የመዘዋወር ንብረት የማፍራት መብታቸው ተጠብቆ እየኖሩ ባሉበት እኛ ተለይተን አፋኝና የህዝብን መብት የሚጋፋ ደንብ እያወጣን ለማስተዳደር የማይቻልበት ድረጃ ነው የምንደርሰው።ዓለም እራሷ እየጠበበች ነው የመጣችው መንግስት በዚህ ሁኔታ ይቀጥላል የሚል እምነት የለኝም። ቢወድም ባይወድም የውስት ሁኔታው ሲገፋው የዓለም ሁኔታ አስገዳጅ ሀኔታ ውስጥ ይከተዋል ብዬ እገምታለሁ።

ጥያቄ: አሁን እያየን ያለነው ግን ተቃራኒውን ነው

መልስ: አሁን ሲታይ የሚወጡ ህጎች ሁሉ ወደፊት ስልጣን ላይ ይመጣሉ ተብለው የሚታሰቡ አካላትን ለመገደበ ሆን ተብለው የሚወጡ ናቸው።ግን በእኔ አመለካከት ህጎች ራሳቸው ናቸው የሚያጋልጡት።ህጎች በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ሲታዩ በዓለም ሀገራትና መንግስታት ሲታዩ ገዳቢ በመሆናቸው የሞራል የኢኮኖሚም፤የፖለቲካ ተፅኖ ማሳደራቸው አይቀርም::

ጥያቄ: ሠላማዊ ትግል ለማካሄድ የሚስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች እየተዘጉ፤ ክልከላና ማዕክላዊነት እየተጠናከረ በመምጣት አንዳንዶች ተስፋ ቆረጠው አማራጭ በሚፈክጉበት ሁኔታ እናንተ ለሰላማዊ ትግል ታማኝ የሆናችሁት ምን ተስፋ ቢታያችሁ ነው?

መልስ: የህዝባችን ንቃት እያደገ ነው የመጣው ብዬአለሁ። የዓለምን ሁኔታ የሚያዩበት ስለመብታቸው የሚጠዩቁበት ደረጃ ላይ ነው ያለነው። ይህ መንግስት ከሚፈልገው በላይ ሆኖል። ይሄ ለሰላማዊ ትግሉ ረዳት ነው። ህዝብ ስለነፃነቱ ስለመብቱ፣ ስለግዴትው ያለው እውቀት እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለሰላማዊ ትግሉ አስተዋፆ እያበረከተ መሄዱ አይቀርም። የፖለቲካ መልክቶችም በቀላሉ የሚረዳበት ሁኔታ ስላለ ተስፋ የምንደርገው ህዝባችንን ነው።

ጥያቄ: የተቃውሞ ፖለቲከኞች እርስ በርስ መናቆር መለያየት እንጂ አብረው ለመስራት አልታደሉም በዚህ ሁኔታ ኢህአድግን ማሸነፍ የሚቻል ይመስሎታል?

መልስ: በሀገራችን ረጅም ሰላማዊ ትግል ልምድ አላዳበርንም። ይያካበትነው ልምድ በጣም ትንሽ ነው። በዚህ የተነሳ ሊሆን ይችላል አብሮ ለመስራት ያልተቻለው። ባለን ትንሽ ልምድ ተመስርተን ልዩነታችንን አጥብበን ለህዝብ የሚጠቅም ሥራ መሥራት ይኖርብናል። ልዩነታችንን አቻችለን በሚያቀራርቡን ጉዳዮች ላይ በመስራት ህገወጥ አሰራርን በህግ ሽፋን የሚሰራ አምባገነን ለመታገል ማበር ይጠበቅብናል። አንዳንድ እንቅስቃሴዎች እየተካሄዱ ነው። አሬውም በቅርቡ ይታያል የሚል እምነት አለን።

ጥያቄ: አንድነትን ከመቀላቀላችሁ በፊት ከኢንጅነር ሀይሉና አየለ ጫሚሶ ቡድን ጋር ለመደራደር አልሞከራችሁም? ከሞከራችሁስ ለምን ሳይሳካ ቀረ?

መልስ፡ ከማንም ጋር አልተደራደርንም። አመራሮች እስር ቤት ሲገቡ የሞከርነውን ቦታ ሲፈቱ ለማስረከብ ሞክረናል። በቃላችን መሰረትም ከስር ቤት እንደወጡ ሁሉንም ግብዣ ጠርተን አመራሩን ለማስረከብ ተዘጋጅተን ነበር። ከነሱ ውስጥ የራሳቸውን ሀሳብ ያራመዱና የወጡ አሉበት። በአብዛኛው ግን የዲሞክራሲ ሂደቱ እንዲቀትል የፈለጉት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ውስጥ ወደፊት በመቀጠል ላይ ናቸው።

ጥያቄ: እንዴት አንድነትን መረጣችሁ?

መልስ: አንተ በአነጋገርህ እዚህ ውስጥ ጨመርካቸው እንጂ አቶ አየለ እዚህ ቁጥር ውስጥ የሚገቡ አይደሉም። ኢንጅኒየር ሀይሉም በውጭ ሀገር ነበሩ። እነብርቱካን እዚሁ ሀገር ውስጥ ስለነበሩ በምናደርገው የዲሞክራሲ ትግል ለምቀጠል ተስማምተን እየሰራን ነው። ይሄ ማለት በሌሎች ላይ በሩ ዝግ ነብር ማለት አይደለም።ሁሉም በዚህ ሂደት መካፈል ለሚፈልጉ ጥሪ ተደርጎ የመጡ መትትዋል።

ጥያቄ: አንድንት አሁን ምን እይሰራ ነው?

መልስ: አንድንት ከተቋቋመ አንድ ወር ገደማ ሊሆንው ነው። በዚህ ግዜ ውስጥ የአማካሪ ምክርቤቱን ለሦስት ግዜ ጠርቶ የፖለቲካ ፕሮግራሙን ምንም ክፍተት በማይሰት መልኩ አሻሽሏል።አመራሮችን ፤ ንኡስ ኮሚቴዎችን መርጠል። አስፈላጊ ዶክመንቶችን ለምርጫ ቦርድ አስገብቶ እየተጠባበቀ ነው።

ከዚህ በተጓዳኝ ሰላማዊ ትግሉ በምን መንገድመቀጠል አለበት በሚለውና ለዴሞክራሲ ግንባታ መጠናከር በሚደረገው ትግል የአመራሮቻችንና ያባላቶቻችንን አቅም ለማሳደግ የተለያዩ ወርክ ሾፖችንና ስልጠናዎችን ለመስጠት ዝግጅታችንን አጠናቀናል።

አትላነታ * ቦስተን * ችካጎ * ዳላስ * ዴነብር * ሎሳንጀለስ* ላስሸገስ * ሚኒያፖልስ * ናሽቪል * ኦክላነድ * ኦሃዮ * ፊኒክስ * ሳንሆዜ * ሲያትልን * ደቡብ ዳኮታ * አፐ ስቴኢት ኒኦርክ * ዋሽንግትን ሜትሮ

የቅንጅት ለአንድነት ለዲሞክራሲ በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች መህበር
766 Rock Creek Church Rd., NW .Washington DC, 20010 *ስልክ (202) 541-0556
ፋክስ: (202) 541-0557.*ኢሜል: kinijitna@kinijitna.org
Www.kinijitna@kinijitna.org

አስተያየቶን በ awdeethiopia@gmail.com ይጻፉልን